M05/1/A1AMH/HP1/AMH/TZ0/XX
22050013

**AMHARIC A1 – HIGHER LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU SUPÉRIEUR – ÉPREUVE 1**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL SUPERIOR – PRUEBA 1**

Tuesday 3 May 2005 (morning)
Mardi 3 mai 2005 (matin)
Martes 3 de mayo de 2005 (mañana)

2 hours / 2 heures / 2 horas

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N’ouvrez pas cette épreuve avant d’y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire sur un seul des passages.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento.

**ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ አስተያየትህን ስጥ(ስጭ)፡፡**

**1. (ሀ)**

## ከአክሱም ጫፍ አቁማዳ

ትግራይ ላከ ወሎጋ አበድረኝ ብሎ አንድ ቁና
ጤፍ
ወሎም አፈረና የለኝም ማለቱን ባህሉን መዝለፍ
ቆሌውን መንቀፍ
ላከ ወደ ሸዋ ምናልባት ቢሰጠው ለሰው
እሚተርፍ፡፡
ሸዋም አፈረና የለኝም ማለቱን ወደሐረር ዞረ
ሐረርም መልሶ ባሌን አተኮረ
ባሌም ወደአርሲ፣ አርሲ ሲዳሞን
ሲዳሞም ተክዞ፣ግን የለኝም ብልስ ማን ያምነኛል
ብሎ
ወደጋሞ ላከ አቁማዳ ጠቅሎ፡፡

ጋሞን ብርድ መታው ሐዘን ገባውና
የራሱን ምንዳቤ የግል ስቅየቱን ችሎት በጥሞና
በጋቢ ደቡኖ የልቡን ጠባሳ ሲኖር እንደደህና
ዛሬ የወንድሙን የእርዳኝ አቤቱታ መስማት
አልቻለና፡፡
አውጥቶና አውርዶ ላከ ወደ ከፋ እጅግ አስተዛዝኖ
ከሀፍረት ያድነኛል፣ ከረሀብ ያወጣኛል ሲል
ባያሌው አምኖ፡፡
ከፋ እንደደረሰው በድንገት አቁማዳው በነብሱ
ዋይታ
ሐራራው ተሰማው የሥጋው ድንፋታ
በብልሀት አዛጋ ቆይቶ ቆይቶ የተስፋ ጠል ቀዳ
ሲልክ ከኢሉባቦር አበድረኝ ብሎ እህል በአቁማዳ፡፡
ጭምቱ ኢሉባቦር ይኖር የነበረ የቤቱን ጉድ ጓዳ
በሞኛሞኝ ገላው ቆዳው ውስጥ ወሽቆ
ጠየቀ ወለጋን ሐፍረቱን ደብቆ ኩራቱን ዘቅዝቆ፡፡
ኬት አመጣ ብሎ ወደኔ ላከብኝ እያለ ወለጋ
እጅጉን ተደሞ
ሄደ ወደጎጃም ዛሬን ሁነኝ ብሎ ሊማፀነው ቁሞ፡፡
ጎጃምም ተሰምቶት፣ ሰቀቀን ሐዘኑ፣
ደረት እየመታ፣ ቅኔ እያወረደ፣ እንባ እያፈሰሰ
ወግና ኩራቱን በየቦዳው መሀል እየነሰነሰ
ዐባይን ተሻግሮ ከጎንደር ደረሰ፡፡
ፋሲል ላይ ተነጥፎ፣ ጎንደርም ሐዘን ላይ ነበረ
ተቀምጦ
ተድላ ልጁ ሙቶ፣ ገናን ክንዱ ታጥፎ፣ በዘመን
ተድጦ

ጎጃም መጣ ሲሉት የእዝን የተመኘን ልቡን
    በታዘበ
የኩራት ካባውን ሲጥል ባንጓበበ
የወንድሙ መምጣት፣እቅጩ መንስዔ፣መሆኑን
    ሲረዳ ረሀብ አበሳ
ጥንትም አልሆነኝም ከእንግዲህ ይበቃኛል
    ለይሉኝታ አልሳሳ
ብሎ ከኤርትራ እህል ለመበደር በርትቶ ተነሳ።

የዘመዱ እጦት ነበረና እጦቱ በዝቶ ሰቀቀኑ
ኤርትራ ታመመ ደም ጎረፈ ከዓይኑ
ወደትግራይ ላከ መላ ባገኝ ብሎ ከአደራ ደብዳቤ
"እባክህ ላክልኝ አንድ አቁማዳ እህል ልሞት ነው
    ተርቤ።"

ደበበ ሰይፉ፡ <u>ለራስ የተፃፈ ደብዳቤ</u> ሜጋ ማተሚያ ቤት፡ **1992።**

የዚህ አይነት መልክ ያለው ውሻ ባዳኝነቱ የታወቀ ነው ። አጭር ምንሽሬን አቋምጬ ይገ[illegible] ስራመድ በደም ፍላት ነው ። አስር ጊዜ በአእምሮዬ የሚመጣብኝ፡—

‘ወረታው ተበጀ ምን ወንድም አለው ፤
እንደ አህያ ሬሳ ወድቆ የቀረው’

የሚለው ነው ።

“እንዲሁ ጫካ ለጫካ ስል ውዬ ማታ ስገባ አባቴ ተመደቡ ላይ ተቀምጦ ጥሬ መሳይ ይቆረጥማል ። እንደምን ዋላችሁ ስል መልስ አልሰጠኝም ። እናቴ ብቻ ፣ ‘እንደምን ዋለህ ልጄ!’ አለችኝ ። ሃዘን አጥንቷን ሰብሯታል ። ተሞተው ልጅዋ የበለጠ ለኔ ትመሽካለች ፤ ትደቃለች ። ቶሎ ብላ እንጀራ አቀረበችልኝ ።

“ለውሻውም ስጪው” ስላት ፣ አባቴ ቀበል ብሎ ፣ ‘አብረሽ አቅርቢላቸው! የውሻ ጓደኛ አበጅቷል ። አየ ነዶ መሞት!’ አለ ።

‘ምነው ዝም ብትል ፤ ምን አድርግ ነው የምትለው ? ጓደኛውን ፣ ወንድሙንማ ገለውበታል ። ይህንም አትቸኩል’ አለችው ፣ እናቴ እንባዋን እያፈሰሰች ። አባቴ ዳግመኛ አልተናገረም ። እኔም እርቦኝ የነበረው በነገር ሲወጋኝ ጊዜ ወስፋቴ ተዘጋ ። እጄን አባብሼ ፣ አንገቴን ደፍቼ ተቀመጠሁ ። ንግግር የሚባል ነገር የለም ። ቤቱን ዝምታ ዋጠው። ቤተሰባችን ሰላም ያጣው ወንድሜ ተሞተ ወዲህ ነው ።

አንዳርጌ መስፍን: <u>ጥቁር ደም</u>: ቦሌ ማተሚያ ቤት ፣ 1988::

---